# መሳለሚያ

## የጎፈር አለንጋና ክቡር ህሊና

*ቁም ነገር ነው እንጂ ለሰው ልጅ ዘመዱ*

*መች ይሸኛል ወዳጅ ርቀው ሲሄዱ*

*ፀሐይ መስፍን*

*ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው*

ሀይረዲን አብዱልከሪም

### ክፍል አንድ

አዲስ አበባ አማኑኤል መሳለሚያ መጠሪያውን ማን እንደሰጠው በርግጠኝነት መናገር ባልችልም ቦታው ከኮልፌ አጠና ተራ፣ ከእህል በረንዳና ከከ/ሀገር አውቶቡስ ተራ የሚመጡት መንገዶች የሚገናኙበት መስቀለኛ ሥፍራ ሲሆን ወደ ደቡብ እስከ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣ ወደ ሰሜን ምዕራብ እስከ ዘነበ ወርቅ ድልድይ፣ ወደ ምሥራቅ ደግሞ እስከ ቀድሞው ልዑል መኮንን ት/ቤት፣ ወደ ሰሜን እስከ አዲሱ ሚካኤልና ኳስ ሜዳው የሚዘልቅ ሰፊ አጎራባች ክልል ይጠቀልላል። አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ ከዘመን ወደ ዘመን እያሽቆለቆለ በሚሄድ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ለፍቶ አዳሪ ሲሆን በዘመነ ወያኔ ወደዚሁ የድህነት ክልል ባስደናቂ ፍጥነት በመገስገስ ላይ ያለ ቀደም ሲል በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበረ ነዋሪም ይገኙበታል። የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣ የሳንባ ነቀርሳ ክሊኒክ ፣ የቢላል መስጊድ፣ የአእምሮ ህሙማን ሆስፒታሉና እህል በረንዳው በመሳለሚያ ዙሪያ የሚገኙ መለያዎቹ ናቸው ። መሳለሚያ የታላቁ መርካቶ መግቢያ በርና መሸጋገሪያ ሲሆን ያብዛኛው ነዋሪም ህይወት ከመርካቶ ጋር የተሳሰረ ነው። ነባሮቹ የወሆን ሰገድ፣ ቀስተ ዳመናና ቢትወደድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች መሳለሚያ ከከተሙ ዘመናት የተቆጠሩ ሲሆን በአካባቢው ተወልዶ ላደገ ከነዚህ ት/ቤቶች ባንዱ ማለፉ ምናልባትም የጎፈርን አለንጋ መቅመሱ ቢያንስ ደግሞ ስለጎፈር በሰማው አስፈሪ ታሪክ በወሰን ሠገድ ት/ቤት በራፍ ሲያልፍ ልቡ በፍርሀት መራዱ የማይጠበቅ አልነበረም። ጎፈር የወሰን ሰገድ ት/ቤት ዘበኛ ሲሆኑ ወሰን ሰገድ ሲነሳ እሳቸውን አለማስታወስ ከቶ አይቻልም። ጎፈር ወሰን ሰገድ ናቸው። መምህራን መቅጣት ሲሰለቻቸው ወይም በጣም አስቸጋሪ የሚሉት ተማሪ ከገጠማቸው ለጎፈር አሳልፈው ይሰጡታል። ለዛ ተማሪ ያች ቀን ርጉም ናት። በየወቅቱ የት/ቤቱ አስተዳደርና ርዕሰ መምህራን እንኳ ሲቀያየሩ የጎፈር የቅጣት ባህርይና ፖሊሲ አይቀየርም ጎፈር ራስ ገዝ ናቸው ከወሠን ሠገድም በላይ። መደበኛ ስማቸው ማን እንደሆነ አብዛኛው ተማሪ የሚያውቀው አይመስለኝም ጎፈር የተባሉት ምናልባት ዘወትር ሚዶ በማያውቀውና እንደ ግዴለሽ አጥር ወጣ ገባና ዘርዘር ብሎ በቆመው ገብስማ ጎፈሪያቸው ምክንያት ይመስለኛል። ለነገሩ ጎፈር የሚለው ስም ከሰውየው በላይ ስለገነነም ተማሪው መደበኛ ስማቸውን አለማወቁ ብዙም አያስጨንቀውም። ባህሪያቸውን መጣኝ ገላጭም ስለሚመስል ስሙን ያፀደቀላቸው ይመስላል። የጎፈር አለንጋ ብዙዎችን አባንኗል የዚህ አጭር ማስታወሻ ምክንያቶች የሆኑትን ተሻለንና ፀጋዬንም ጭምር። ይሁን እንጂ የጎፈር አለንጋ ኋላ ላይ በታላቅ ጀግንነታቸውና ፅናታቸው ገዳዮቻቸውን ሳይቀር ያስደነቁና ያስደነገጡ ወጣቶችን ለቀጣዩ የቀይ ሽብር ጣዕር አላዘጋጃቸውም። ጎፈርን ያስናቁ ያስረሱም ማለት ይሻላል እጅግ ብዙ አረመኔዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ተቀፍቅፈው ሀገር በቀላሉ ልትተካው ያልቻለች አንድ ድንቅ ትውልድ እጅ በጅ አርደው ከምድር በታች አውለዋል። ብዙዎች የጎፈር አለንጋ የአባትነት እንደነበረም ያስተዋሉት ዘግይተው የቀይ ሽብሩን ገራፊዎች ንክ ባህርይና አውሬነት ካዩ በኋላ ነበር። ጎፈር ምን ቢጨክኑ ቅጣታቸው ከእርማት አያልፍም። በጎፈር አለንጋ ልቡ ይርድ የነበረው ወጣት ዘመኑ ደርሶ ከታሪካዊ ተልዕኮው ጋር ሲገናኝ ለሚወደው ህዝብና ለሚያፈቅራት ሀገር ሊነገር በማይቻልና ወደር በሌለው ጀግንነት *በትግል መሞት ህይወትን* እየዘመረ ራሱን ለተራብ አዞ ለፈላ ዘይትና፣ ለሌላም አረመኔያዊ ስቃይ አሳልፎ ሰጥቷል። ሊሸከመው የተገደደው መከራ፣ መከፈል የነበረበትም ዋጋ ነበረና። “ራስን ለወዳጆች አሳልፎ ከመስጠት የሚልቅ ፍቅር የለም” የሚለው ሰማያዊ እውነት ምድራዊ የተደረገበት ታላቅ ታሪክ ነው።

መሳለሚያ ሲወሳ የሚታሰቡ ሌሎች ተጓዳኞች ደግሞ ያካባቢው ወጣቶች ማዘውተሪያ የነበሩት ድምፅ፣ ካሊፎርኒያ፣ሶል ሼክ አትለፉኝና ህይወት ማራኪ ሻይ ቤቶች ናቸው። ዛሬ አብዛኞቹ የሉም ። ስለሻይ ቤቶች ከተነሳ በተማሪው እንቅስቃሴና በተከታዩም ፀረ ደርግ ትግል ውስጥ የነበራቸው ሚና ራሱን የቻለ ትልቅ ታሪክ ይወጣዋል። ከቀይ ሽብሩ ዘመን ቀደም ሲል ጀምሮ በየአካባቢው የነበሩ ሻይ ቤቶች ከጊዜ ማሳለፊያነት አልፎ በመሰባሰቢያ መወያያና መደራጃ ነት አገልግለዋል። በወቅቱ የነበሩ ፖለቲካዊ የጥናት ክበቦች ወጣቱን በፖለቲካዊ ሀሳቦች ዙሪያ ለማሰባሰብና በተለያዩ ርእሶች ላይ ያላቸውን አቋምና የንድፈ ሀሳብ ትንታኔ ጽሁፎቻቸውን ለማሰራጨት ተጠቅመውበታል። አንዋር መስጊድ ፊት ለፊት የሚገኘው ሰላም ሻይ ቤት ለዚህ ዋነኛ ምሳሌ ነበር ማለት ይቻላል። ደርግ ሥልጣን በጨበጠ ማግሥት በህዳር 67 ስድሳዎቹን የአፄ ሀ/ሥላሴ ባለሥልጣናት በመረሸን የጀመረው የቀይ ሽብሩ ፍጅት መጠኑን አሳድጎ የደርግ ነፍሰ ገዳዮች መናኸሪያ ከመሆናቸው በፊትና የህዝቡ ታጋዮች ማደሪያቸውን ወደ ደጀሰላም፣ መቃብር ቤቶች፣ ጫካዎችና ቱቦዎች ማዛወር ከመገደዳቸው በፊት ሻይ ቤቶች በኢሕአፓ ዙሪያ ለሚታገሉ ሀይላት መሸሸጊያ ለትግሉ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን (የሚበተኑ ወረቀቶች) መቀባበያ መሰወሪያ ካካባቢያቸው ለተሳደዱና ማደሪያ ላልነበራቸው ወጣቶች በጊዜያዊ መጠለያነትና መመገቢያነት አገልግለዋል። ይህ ሁሉ ደግሞ ይመቻች የነበረው በሠራተኛው ህቡዕ ድርጅት ኢላአማ ሥር በተሰባሰቡና ትግሉን በተቀላቀሉ የሻይ ቤቶች ሠራተኞች አማካይነት ነው። መርካቶ አካባቢ የሚገኙት ሠላም፣ ነጭ ወንበር፣ አሰብ፣ መሀመድ ሳላህ፣ መቻል፣ ዋንዛ ፣ዕፀ ገነት፣ ልደትና ሌሎችም ካፊቴሪያዎች የሚጠቀሱ ምሳሌዎች ናቸው።

ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ ካብዮቱ ቀደም ብሎ በነበረው የተማሪው እንቅስቃሴ ዘመን ሻይ ቤቶች የዘመኑ ወጣት የድብድብ ቡድኖች መናኸሪያም ነበሩ። ታዋቂና አስፈሪ ከነበሩት የድብድብ ቡድኖች ውስጥ የቻይና ፣ የሸራ ተራ፣ የበረሀ ዘንዶና የእሥራኤል ግሩፖች የየአካባቢያቸው አስገባሪዎች ነበሩ። በማሪዮ ፑዞ “ጎድ ፋዘር” ውስጥ እንደተገለፁት የአሜሪካና አውሮፓ ማፊያ ቡድኖች ስር የሰደደ በግዙፍ ኤኮኖሚያዊ ና ፖለቲካዊ ጉልበት የሚታገዙ ሀያል ቡድኖች ባይሆኑም የኛዎቹም የመንደር ሽፍቶች የየአካባቢያቸውን አቅመ ደካማ ህ/ሰብና ልጃገረዶችን ለማጎሳቆል የሚያንሱ አልነበሩም። እንደማንኛውም ወጣት ሁሉ የነዚህ ስብስብ አባላትም መሰባሰቢያቸው ሻይ ቤቶች ነበሩ። ከሌሎች ባላንጣ ቡድኖች ጋር ፍልሚያ ለመግጠም ወይም ሰለባዎቻቸውን ለማጥቃት የዘመቻ ፕላናቸው የሚረቅበት፣ ከፖሊሶች ማምለጫና መሸሸጊያቸው በያካባቢው የነበሩት ሻይ ቤቶች ናቸው። ሆኖም ግን አገር አቀፉ ህዝባዊ እንቅስቃሴ የወጣቱን ታሪካዊ ተልዕኮና የህይወት አቅጣጫ በመቀየሩ ወጣቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ በብሔራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች መዋጥ ሲጀምር ይህ በውድም ሆነ በግድ የብዙዎችን ቀልብ ተውሶ የነበረውና የህ/ሰብ የዕለት ተዕለት ኑሮ አካል ተደርጎ እስከመታሰብ ደርሶ የነበረው ቦዘኔያዊ ንዑሥ ባህል (Sub culture) ባንድ አዳር አሳፋሪ ወደ መሆን ደረጃ በመውረዱ እነዚህ ስማቸው ሲጠራ ሽብርና ፍርሀትን ይለቁ የነበሩ ቀውጢ ፈጣሪ ስብስቦች ከመቅፅበት ያለምንም አስገዳጅ ሀይል አዲስ በተፈጠረው ፖለቲካዊ አየር ተፅዕኖ ብቻ ሟሸው መኖራቸው እንኳ ወደማይታሰብበት ደረጃ ደርሶ ህልውናቸው ሲከስም አብዛኞቹ የነዚህ ቡድኖች አባላት በመካሄድ ላይ የነበረውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ በመቀላቀል ትግሉ ዓላማ አልባ የነበረውን ቦዘኔያዊ የረብሻ ኑሮ (Rebel with out a cause) አቅጣጫ ሰጥቶ ትርጉም ላለው የከበረ ተልዕኮ እንዲቆሙና ታሪካቸውን እንደገና እንዲፅፉ መንገድ ሆኗቸዋል።

መሳለሚያ ሌላም ብዙ ታሪክ ተከናውኖበታል። የዚህ አጭር ማስታወሻ አቢይ ታሪክም የተፈፀመው እዚሁ መሳለሚያ በሚገኘው ከቀይ ሽብር ዘመን የግፍ ማዕከሎቸ አንዱ በሆነው የከፍተኛ 6 እስር ቤት ውስጥ ነው። ከፍተኛ ስድስት ቀድሞ የምዕራብ ማዘጋጃ ቤት ቅርንጫፍና የእሳት ኣደጋ መከላከያ ቢሮ ከነበረበት ግቢ ውስጥ ይገኝ የነበረ ሲሆን ዘግየት ብለው ከተመሰረቱት የከፍተኛና የቀበሌ እስር ቤቶች ወይም በተገቢ መጠሪያው ኣሳር ቤቶች አንዱ ነበር። ከፍተኛ ስድስት ከሱ ቀደም ብለው ከተቋቋሙት እንደ ከፍተኛ ሃያ ኣምስት ኣይነቶቹ የስቃይ ስፍራዎች ጋር ሲነፃጸር በደርግ ባለስልጣኖቸ ዐይን የሚያስመሰግን የቀይ ሽብር የግድያ ክብረ ወሰን ባያስመዘግብም (የከፍተኛው ገዳዮች ብዙውን ጭፍጨፋ ያካሄዱት ቀይ ሽብሩን በቀደመው “ነፃ ርምጃ” ወቅት በመሆኑ) አያሌ የህዝብ ልጆች የተሰዉብት ብዙዎች በጀግንነት ፍዳ የተቀበሉበት ቦታ ነበር። በዚህ ጽሁፍ ስማቸው የሚወሳው ጥቂቶችና ሌሎችም የህዝብ ልጆች በልጅነት ዕድሜያቸው በቅድመ ቀይ ሽብር ዘመን በዚህ ጽ/ቤት ደጃፍ ሲያልፉና ሲያገድሙ ይህ ስፍራ ወደፊት ኣንድ ቀን ስለእምነታቸውና ስለህዝብ ተቆርቋሪነታቸው ኣበሳና ፍዳ የሚቀበሉበት የስቃያቸው ምንጭ፣ ሬሳቸው ተጎትቶ የሚወጣበት የጣዕር ኣምሳል ይሆናል የሚል ግምት ኣልነበራቸውም ።

ከፍተኛ ስድስት እንደ ሌሎቹ እስር ቤቶች ሁሉ የራሱ የስቃይ አበጋዞች የነበሩት ሲሆን ምናልባትም ዘመኑ ካፈራቸው አያሌ ሰብአዊ አውሬዎች ውስጥ ኮከቦቹ የከተሙት በዚሁ ከፍተኛ ነበር ማለት ይቻላል። የፓርቲና ሊግ አባላትን ከነህይወታቸው በእሳት ያቃጥል የነበረው ፍቃዱ አስቻለው እንዲሁም የከፍተኛ 6 ቀበሌ 24 ነዋሪ የነበረው የደርግ አባል የሻለቃ መኩሪያ ልጅ ቀንደኛው መኢሶን መብራቱ መኩሪያ (በሴቶች ብልት ውስጥ ጠርሙስ ይጠረምስ ነበር) እጅግ ዘግናኝ የሆነውን አውሬነታቸውን ያስመሰከሩት እዚሁ ከፍተኛ ነው። ፍቃዱና መብራቱ ለተመሳሳይ ግዳጅ ወደ ሌሎች ከፍተኞች ሲዛወሩም በምትካቸው ተሾመና ታመነ የተባሉ

የመኢሶን/ወዝ ሊግ ካድሬዎች፣ ናዝሬት ውስጥ በግሉ ከሃምሳ በላይ የኢህአወሊ አባላትን ያረደውና ከደርግ ውድቀት በሁዋላም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ውስጥ ሹመኛ የነበረው ታደለ ፣እንዲሁም አለባቸው የሚባል ኤርትራዊ ካድሬ ስፍራቸውን ተረከበዋል። በቅርቡ አዲስ አበባ የተመለሰው ደቡር በሚለው ቅፅል ስሙ ይታወቅ የነበረው (ሌላው ቀልቤሳ ነገዎ) ብርሃኑ ዳምጤ ና ታምራት ዮሐንስ የተባሉት የመርካቶና አካባቢው የወቅቱ አንጃኞች የዚሁ ከፍተኛ ስድስት ነዋሪዎች ነበሩ። ብርሃኑ ደቡር ለጥቂት ጊዜ አባል የነበረበትን ኢሕአወሊን በመክዳት የደርግ ገራፊና ጠቋሚ በመሆን በመቶዎች ለሚቆጠሩ የፓርቲና ሊግ አባላት ሥቃይና ሞት ምክንያት ሆኗል። ጓደኛው ታምራትም የግንቦት አብዮት በመባል የሚታወቀውን ከርቸሌ የተካሄደውን የፀረ ኢሕአፓ የፍጅት ዘመቻ በመምራት ለበርካታ የኢሕአፓ አባላት ሥቃይና ሞት ምክንያት ሆኗል። የብርሃኑ ደቡር አይነቱ ቀንደኛ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ወደ ሀገር ለመመለስ መድፈር በራሱ ስለሀገራችን ወቅታዊ ፖለቲካ ብዙ ይናገራል።

ከከፍተኛ ስድስት እስረኛ አብዛኛው በኢሕአፓ አባልነት/ ደጋፊነት የተያዘ ይሁን እንጂ በአሻጥረኛ ነጋዴነት እንዲሁም ኋላ ላይ በደርግ ውስጥ በተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ የተያዙ የቀድሞ ገዳይና መርማሪዎችም ይገኙበታል። ደርግ በስህተት እንዳይገድለን በሚል እጅ ሰጥተው የተለየ ክፍል ተዘጋጅቶላቸው ከሌላው እስረኛ የተለየ እንክብካቤ ይደረግላቸው የነበሩ የወቅቱ አንጃ አባላትም የነበሩ ሲሆን እነዚህኞቹ በእስር ቤቱ ቆይታቸው ከመደበኛ መርማሪዎቹ ባልተናነሰ ማናቸውንም አረመኔያዊ ወንጀል ሁሉ ያከናውኑ ነበር። አዳዲስ እስረኛ ሲመጣ ወደነዚህ አንጃኞች ተወስዶ የመጀመሪያው ምርመራና ማጋለጥ የሚካሄድበት ሲሆን ቀጣዩም ምርመራ የሚከናወነው በነዚህ አንጃዎች አስተያየት መሰረት ይሆናል። ባጋጣሚ ከአንጃዎቹ አንዱ የሚያውቃችሁ ከሆነማ መከራችሁ ተራዘመ ማለት ነው። ይህ ወቅት አንጃኞቹ ወደ መደበኛ ገራፊነትና መርማሪነት የሚሸጋገሩበት ለካድሬነትም የሚመለመሉበት የሽግግር ወቅት ነው። እስረኛው ጊዜው እንዲያልፍለት ስቃዩንም ለመርሳት ዘወትር ራሱን በተለያዩ ተግባራት ይጠምድ ነበር። መደበኛ ከሆነው ፖለቲካዊ ውይይት ባሻገር ድራማ፣ ንባብ፣ ክራር፣ መዝሙር፣ ትረካና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከእስረኞች ትዝታ የማይጠፉ አንዳንድ ለየት ያሉ አጋጣሚዎችም ነበሩ። በአሻጥረኛ ነጋዴነት ሰበብ ከተያዙ እስረኞች መካከል ስማቸውን የዘነጋኋቸው አንድ እስረኛ ሞት አፍጦ እየጠበቃቸው የሚቀጥለውን ቀን ለማለፍ እርግጠኛ ባልሆኑበት ሁኔታ የየወቅቱን የሎተሪ ቲኬት ሳያሰልሱ እየላኩ ያስገዙ የነበረ ሲሆን በከፍተኛ የኢሕአፓ አባልነት የሚጠረጠረው ጋሽ መሀመድ ደግሞ ኮስተር ብሎ የረመዳን ፆሙን ስግደቱንና ቁርአን መቅራቱን ተያይዞት ስለነበር እንኳን በኢሕአፓንነት ለመጠርጠር እሱ አጠገብ ፖለቲካም ማውራት እሱን ማስቀየም እስኪመስል ተደርሶ ነበር። ዘዴው ሰርቶለት ተርፎ  መውጣቱን አውቃለሁ። መምህር ተገኝና ንጋቱ እስረኛው መሃል ቆመው ድፍን ሦስት ሰአት “የአማልክት ሠረገላ” (ቻሪየትስ ኦፍ ጋድስ ) እና መሰል ታሪኮችን ሲተርኩ ያፈዛሉ።  የእስር ቤቱ አራጆች በስካር ነብዘው በውድቅት ሌሊት እስረኛውን ከተኛበት ቀስቅሰው የሽብር ቀረርቶዋቸውን እናፍተውተውበት ሲወጡ የሞት ባይኖር ክራር ደርሶ “ቼ በለውን” ሲቀኝ በደረቁ ውድቅት የተሰበረና የተሸበረን  መንፈስ  አነቃቅቶ ያፍንናል፣ ሕዝበ ኢሕአፓም ከስቃዩና መስዋእትነቱ ባሻገር ቀጣዩና አይቀሬ በሆነው  ሕዝባዊ አመፅ  ሙብትና ሰብእናው የተከበረ ግፉዕ ህዝብ ነፃነቱን ሲቀዳጅ ያያል።